# ኤሌክትራ



**“....**ለኔ የሚያሻኝ ምግብ የገዛ ህሊናዬ ነው...”

**--**ኤሌክትራ**--**

ድርሰት፡ ሶፎክሊስ- 401 BC

ትርጉም፡ ድንቅነህ ዘላለም

ነሀሴ **2003**

ገጸ ባህርያት

ፔዳጎጀስ......................................ኦሬስተስን ያሳደገ ሽማግሌ አገልጋይ
ኦሬስቲስ.....................................የሚቹ የሜሲና ንጉሥ አጋሜምኖን ወንድ ልጅ
ኤሌክትራ....................................የአጋሜምኖን ሴት ልጅ
ማይሴናዊት..................................የማይሴና ሴት

ክሪስቶሚስ....................................የኤሌክትራ እህት
ክሊቴምኔስትራ...............................የኤሌክትራ እናት
ኤጅስተስ......................................የሚሴና ንጉሥ

<u>ትዕይንት **1**</u>

ማይሴና ቤተ መንግስቱ አደባባይ

ሥጦታ

ለሰማርያ ፍቃዱ

“....ማን መሆኑንስ ብታውቂ አንቺ ትለምኚው ነበር....”

ዮሐንስ 4፡10

ፔዳጎጀስ

የቀድሞው የትሮይ ጀኔራል አጋሜምኖን ብቸኛ ወንድ ልጅ ኦሬስቲስ!እነሆ እዚህ ደርሰሃል።ሁሉንም ነገር አውቀሃል።ልብህ ዘወትር ሲጓጓለት የነበረው ነገር ደርሷል።

የግፍ ታዳኟ ልጅ መቃብር የሆነችው አርጎስ እነኋት። ይሄ የተኩላ አዳኝ አማልክት አደባባይ ነው።በዚህ ደግሞ በስተግራህ ዝነኛው የሄራ ቤተ መቅደስ ነው።ይህቺም የትውልድ ሃገርህ ሚሲና ናት።ይሄም ከፊትህ ያለው ሞት ጥላውን የጣለበት ያአባቶችህ መኖሪያ ቤተ መንግስት ነው። በአንድ ወቅት ገና አባትህ እንደተገደለ ደሟን ከደምህ ከቀዳችው እህትህ ከኤሌክትራ እጅ ተቀብዬህ ወደ ሩቅ ሃገር ወሰድሁህ። ህይወትህንም አትርፌ ዛሬ ለበቀል እስከጠነከርህበት ጊዜ አደረስሁህ። እንግዲህ ኦሬስቲስ አንተም ወዳጁ ፒላደስ ምን እንደምትሰሩ ምከሩ። እነሆ ጸሃይ መስረቅ ጀምራለች። አእዋፍም መዘመር ይዘዋል። ጽልመት የለበሰው የሌሊት ኮከብም አልፏል። ሰው ከቤቱ ወጥቶ እግሩን ወደ መንደር ከመሰንዘሩ በፊት አሁን ለተግባር ታላቅ ጊዜ ነው።

<u>ኦሬስቲስ</u>

የተከበርከው የአባቴ ባለሟል ለኖርህበት ቤተሰብ ያሳየኸው ከበሬታ የበዛ የጨዋ ተግባር ነው። ያለፉት አስከፊ ጊዜያት እንኳ ተግባርህን አልለወጡትም። እነሆ ህይወቴን አተረፍሃት። ባንተ እርዳታ ለዚህ በቃሁ። ወዲህ የመምጣቴ ሰበብም አንተ ነህ። ለዚህም የተግባሬን እቅድ ላንተ እገልጣለሁ። አንተም ለሃሳቤ ጆሮህን ስጥ። ምልህንም አድምጥ። መስመር ከሳትሁም አርመኝ።የአባቴን ገዳዮች ተበቅዬ ደሙን ለመመለስ ወደ ፒቶ የአማልክት ስፍራ ስሄድ ይህን ቃል ተናገሩኝ። በእጅህ ጦር፣ ጋሻ ወይም ፍላጻ አትውሰድ፣ ራስህን ብቻ ይዘህ ሂድ። የእጅህም ጥበብ የጦር መሳሪያ ይሁንህ። አሁን የአማልክቱን መልእክት አብረን ሰምተናል። ሁኔታዎች ሲፈቅዱልህ አንተ ወደዚህ ቤት ሂድ።በዚያም የሚደረገውን አጥና። የጥናትህንም ውጤት ለኛ ዘግብልን።እነሆ አንተ ሸምግለሃል። ጊዜውም በጣም ርቋል። ስለዚህ አያስታውሱህም። በዚህ ብርማ ሽበትህ የተነሳም አያስታውሱህም። ሄደህ የምትነግራቸውም ታሪክ ይሄውልህ። ከፎሺያዊው ሸሪካቻ ከፍኖታሽ ዘንድ የተላክህ መልእክተኛ መሆንክን ንገራቸው። እንም በኔ በኦሬስተስ ላይ የወደቀውን ድንገተኛ የሞት አደጋ አብስራቸው። በመሃላም አረጋግጥላቸው። የአሟሟቴን ሁኔታ እንኳን ቢጠይቁህ በፒቲያውያን የሰረገላ ውድድር እጅግ ከፈጠነ ሰረገላ ወድቆ ተቆራርጦ ሞተ በላቸው። እኛ ወደ አባቴ መቃብር ሄደን ህጉ በሚፈቅደው መንገድ ከችፍርግ ጠጉሬ በተቆረጠ ዘለላ ለሙት የሚገባውን መስዋእት እናቀርባለን።ስንመለስ ቀድሞ በጫካው ውስጥ የደበቅሁትን የነሃስ ሳጥን ይዘን እንመጣለን። በዚህም እጅግ የሚያስደስታቸውን ዜና እናበስራቸዋለን። በሳጥኑ ውስጥ ያለው የኦሬስተስ በድን አመድ ነው እንላቸዋለን።በአካል ከሞትሁ መኖሬን ምን ያስጠረጥራቸዋል። ከዚህ ቀደም በቃላት ሞታቸው ተነግሮ ህያው ሆነው በክብር ወደ ቤታቸው የተመለሱ ሰዎችን ታሪክ አውቃለሁ። እናም በመሃሉ ሞቴ የተነገረው እኔ ዳግም በአባቴ ቤት

በጠላቶቼ ላይ እንደ አጥቢያ ኮከብ እበራለሁ።አንቺ የአባቴ ሀገር ምድር እናንተም የአባቴ አማልክት በቸር ተቀበሉኝ።በድል አጎናጽፉኝ።አንተም የአባቴ ቤት ስትጠብቀኝ የነበርኩት ሰው መጥቻለሁና አታዋርደኝ። ይሄው ነው የምለው ያለኝ። ታላቁ ሰው በል ወደ ተግባርህ ተሰማራ እኛም ወደ ስፍራችን ለመሄድ ወቅቱ አሁን ነው። ወቅታዊነት የተግባር ሁሉ ንጉሥ ነው።

(ኤሌክትራ ከውስጥ ስትጮህ ትሰማለች)

ፔዳጎጀስ

ከቤት ውስጥ ከአገልጋዮች አንዷ ትመስለኛለች የምትጮኸው።

ኦሬስቲስ

ያልታደለችው እህቴ ኤሌክትራስ ልትሆን አትችልም? እዚህ ቆይተን ለቅሶዋን እንስማ?

ፔዳጎጀስ

የለም። ከታዘዝነው አስቀድሞ ምንም መምጣት የለበትም።ሁሉም የሚጀመረው ከዚያ ነው። መጀመሪያ ለአባትህ መስዋዕት ማቅረቡ ወደ ድል ያመራናል።

(ይወጣሉ። ኤልክትራ ትገባለች)

ኤሌክትራ

የተቀደስከው ብርሃን! አንተም የምድር ባልደረባው ነፋስ! እስከደማ የተጫነኝ ሀዘን ምን ያህል ከባድ ነው! የለሌሊት ጨለማ ሲሄድ እንዴት እንደጮህኩ ሰማችሁ? ሌሊቱን በእድለ ቢሱ አባቴ ሞት ሳነባ ለማደሬ በእንባዬ ሲርስ የሚያድረው መኝታዬ ምስክሬ ነው። የገደለውኮ የባእድ ሃገር ሰው ወይ የአማልክት እጅ አይደለም። የእናቴና አልጋዋን የሚጋራት ሰው መሰሪ መጥረቢያ ነው ከግንዱ እንደሚገነጠል ቅርንጫፍ የዘነጠለው። ለዚህም ከኔ በስተቀር ለሙታን የሚገባ ሃዘን አልተደረገለትም።ምንም አልተለቀሰልህም አባቴ! እኔ ግን የሌሊት ኮከብና የቀን ብርሃንን የሚመለከት ዐይን እስካለኝ ድረስ ስላንተ ማልቀሴን አላቋርጥም።ሰቀቀኔን መላው ዓለም እስኪሰማኝ እጮሃለሁ። የሙታን ዓለም አማልክት የእመቀመቃት አማልክት እናንተ በግፍ የተገደሉትን ሁሉ የምታዩ ኑና የአባቴን ሞት ተበቀሉ። እንዲረዳኝ ወንድሜን ወዲህ ላኩልኝ። የተጫነኝን በደል ብቻዬን ለመፈንቀል የሚበቃ ዐቅም የለኝም።

(ማይሴናዊት ትገባለች)

ማይሴናዊት

ኤሌክትራ! አንድ ጊዜ በመሰሪዋ እናትሽ እጅ ለሞተው መልካሙ አባትሽ አጋሜምኖን ስለምን ታለቅሻለሽ? ስነ ስርዓቱን ማክበር ካለብሽ የሱ ሞት የከፋቱ ሁሉ ማብቂያ ይሁን።

ኤሌክትራ

እውነተኛዋ ወዳጄ ልታጽናኚኝ መምጣትሽ ነው? የምትናገሪውን አውቃለሁ። አንዱም አይጠፋኝም። ግን የሚለወጠወ ነገር የለም። ለሞተው አባቴ አሁንም ቢሆን በግፍ ለሞተው አባቴ ማንባቴን አላቆምም።

ማይሴናዊት

ግንኮ ሁሉን ከሚውጠው የሞት ሃይቅ ልታወጭው አትችይም።

ኤሌክትራ

በግፍ የሞተ ወላጁን በቀላሉ የሚረሳ የቀለለ ሰው ነው። ለሃዘኔ ይበልጥ የሚስማማው እንደ ንጋት ወፍ ፂው ፂው የሚል የለቅሶ ዜማ ነበር። ለዘለዓለም መቃብር ላይ ታለቅስ እንደነበረችው ናዮብ እንባ ነበር ሃዘኔን የሚመጥነው።

ማይሴናዊት

በአንቺ ብቻኮ አይደለም ይሄ ሀዘን የመጣው! ሃዘኑ የደም ቅጅ የሆኑት ዘመዶችሽ ሁሉ ነው።ለምን ያንቺን ብቻ ሀዘን ታጎይዋለሽ? ክሪስቶሚስ፣ አይፍጂንያ፣ ያም በስደት ያለውና አንድ ቀን ወዲህ መምጣቱ የማይቀረው ምስኪን ወንድምሽ ኦሬስቲስም የሃዘኑ እኩል ተጎጂዎች ናቸው።

ኤሌክትራ

እድለ ቢስነት እያላጋኝ የልጅ ወልዶ ማሳደጊያ ጊዜዬ እስኪያልፍ በሃዘን ጠብቄዋለሁ። እሱ ግን በቀሉን ረስቷል። ከሱ ምን መልእክት መጥቶልኝ ያውቃል? እርግጥ ሁሌ ለመምጣት እንደጓጓ ነው። ግን እስካሁን አልመጣም።

ማይሴናዊት

ሁሉን ከላይ ሆኖ የሚያይ ዚዩስ አለ። አንቺ ብቻ ተረጋጊ። መገፋትሽን ለሱ ብቻ አመልክቺ። ጠላቶችሽን ደርቀሽ አትታገያቸው። ፈጽመሽም አትርሻቸው። ጊዜ

ሁሉም ደገኛ አምላክ ነው። ባህር ማዶ ያለው ወንድምሽም ሆነ ባህርን የፈጠረ አምላክ ዝም አይሉም።

ኤሌክትራ

ለኔ ግን አብዛኛው እድሜዬ ያለ ተስፋ አልፏል። የቀረኝ ተስፋ የለም። ልጅ አልባ አልፌያለሁ። እንደ ነውረኛ መጻተኛ በአባቴ ቤት ቆሜ ቀርቻለሁ።

ማይሴናዊት

ሀዘንሽ ያንሰፈስፋል።በተሳለ ፋስ የሞተው አባትሽ ሞትም አሰቃቂ ነው።

ኤሌክትራ

ይህ ከሆነበት ቀን ይበልጥ የከፋ ቀን ለኔ ከቀናት መካከል የለም። ወዮ ያ ቀን ከቁጥር የከፋ በደል የተፈፀመበት ምሽት ምንኛ አስፈሪ ነበር። ይህን በደል በፈጸሙት ላይ እሱ ፈጣሪ ብድሩን ይከፈላቸው።

ማይሴናዊት

ድምጽሽን ቀነስ አድርጊው። በሩቅ እስኪሰማ ድረስ አትጮሂ። ከምንተግባር የተነሳ እንደምትሰቃዩ አታውቂም? እድለ ቢስነትን አንዴ ከአምላክሽ ተረክበሻል።ከሃያላኑ ጋር እንዲህ ያለውን ጠብ እጅ ለእጅ ልትጋፈጭ አትችይም።

ኤሌክትራ

ከነበርሁበት ሽብር ወደ ሌላ ሽብር እየተገላበጥኩ ነው። የገዛ መንፈሴን አውቀዋለሁ። ከዚህ ሃዘኔ ከቶም ልገታ አልችልም። ምን የሚያበረታ ቃል አለ ብለሽ ነው? የስቃይ ህመም መፈወሻ የለውም።

ማይሴናዊት

ይህንን የምነግርሽ ልጄ ከሰቆቃ ወደ ባሰ ሰቆቃ እንዳትገላበጥባት እንደምትሻ እናት ነው።

ኤሌክትራ

ለኔ ሰቀቀን የተፈጥሮ መለኪያው ምን ይሆን? ሚጆች እንቆቅልሽ ሆነው ሳለ ነገሩን መርሳት ክቡር ነገር ነው? ከቶ እንዴት ያለ ሰው ነው ይሄን መርሳት የሚችለው?

መቼም እንዴትም ቢሆን ይሄንን መርሳት አልችልም።የገደሉት ሁሉ ፍትሃዊ ሞት እስኪሞቱ ድረስ የኔ እንባ ማቆሚያ የለውም።

ማይሴናዊት

ወደዚህኮ የመጣሁት በልቤ ቅንነት ብቻ ነው። ያለበለዚያ ሃሳብሽን ግልፅ አድርገሽ ንገሪኝ። እኔም እታዘዝሻለሁ።

ኤሌክትራ

እንደተራ ሃዘንተኛ አድርገሽ ብቻ ከሆነ ያየሽኝ አሳፋሪ ነገር ነው። ይቅርታሽ አይለየኝና የማደርገውን አደርጋለሁ። በመልካም አስተዳደግ ያሳደጋት አባቷእንደሞተባት ሴት ነው የምተክዘው። ከሁሉ የከፋው እድሌ ደግሞ ያቺን የተረገመች እናቴን እለት እለት አያታለሁ። የገዛ አባቴን ልብስ ለብሶ የአባቴን በትረ መንግስት ጨብጦ በአባቴ አልጋ ከእናቴ ጋር ምናልባትም እናት ማለት ካለብኝ ከእናቴ ጋር ከሚዳራው ኤግስተስን ማየቴ ምን ዓይነት ቀን የማሳልፍ ይመስልሻል። ይህን ከይሲ ሰው ብላ አብራ ስታድር ምንም ዕፍረት አይሰማትም። አባቴን በገደለች እለት ለአማልክት የምስጋና መስዋዕት አቀረበች። ልቤ የፈቀደውን ያህል እንኳ ማልቀስ አልችልም። “ አንቺ የተረገምሽ ፍጥረት! ፈጣሪሽ እንኳ የጠላሽ! አባቷ ሞተባት ሴት አንቺ ብቻ ነሽ? ከአንቺ ውጭ ሃዘን የገባው የለም?ርግማኔ በላይሽ ይውረድ! የእመቀመቃት አማልክት አሁን ካለሽበት ሃዘን ለዘላለም አያውጡሽ!” ትለኛለች። የኦሬስቲስን መምጣት ከአንድ ሰው አፍ ካልሰማች ዘወትር ርግማኗ ይሄ ነው።ስለሱም የተነሳ እንደሆነ ወገቧን አስራ “ ለመጥፋቱ አንቺስ ሃላፊ አይደለሽም! ኦሬስቲስን ከእቅፌ አውጥተሽ የወሰድሽው አንቺ አይደለሽም! ለዚህ ተግባርሽም ዋጋ እንደምትከፍዪ እርግጠኛ ሁኚ!” ትለኛለች።

ማይሴናዊት

እስቲ አሁን እንደምታድጊው አድርገሽ ንገሪኝ። ኤግስተስ ከዚህ አካባቢ ነው ወይስ ወደ ሩቅ ቦታ ሄዷል?

ኤሌክትራ

የለም በዚህ ስፍራ አይደለም። እሱ ነእዚህ ስፍራ ቢኖር ኖሮ እኔን እዚህ ቦታ ትገኛለች ብለሽ አታሰቢ። ወደ ርስቱ ስፍራ ሄዷል።

ማይሴናዊት

እንግዲያው እኔና አንቺ በቅን መንፈስ መነጋገር እንችላለን።

ኤሌክትራ

አሁን እዚህ ስፍራ የለም። ምን ነበረ ልትነግሪኝ የፈለግሽው?

ማይሴናዊት

እስቲ ስለ ወንድምሽ ንገሪኝ። እየመጣ ነው? ያመነታል? ወይስ ምንድነው? ይህንን ነው ለማወቅ የፈለግሁት።

ኤሌክትራ

እሱማ እመጣለሁ ነው የሚለው። የሚለውን በተግባር አሳይቶ ግን አያውቅም።

ማይሴናዊት

ትልቅ ነገር የሚሰራ ሰው ሁሉ ማመንታቱ አይቀርም።

ኤሌክትራ

እኔ ግን ህይወቱን ሳድንለት አላመነታሁም።

ማይሴናዊት

እመኚኝ ወዳጁን የሚረዳ መልካምና ቀና ሰው ነው

ኤሌክትራ

አምንሻለሁ። ይሄንን ባላምንማ እስካሁንም በህይወት ባልኖርኩ ነበር

ማይሴናዊት

አሁንም ቢሆን ምንም ነገር አትበይ። እህትሽ ስትመጣ አያታለሁ። የደምሽ ደም የእናትሽ ልጅ ክሪስቶሚስ የሜሮን ፈሳሽ ለዓማልክቱ ለመሰዋት ይዛ እየመጣች ነው።

*(ክሪስቶሚስ የሜሮን መስዋዕት ይዛ ትገባለች)*

ክሪስቶሚስ

ምን ለማለት ነው ወደዚህ የመጣሽው እህቴ! በዚህ ጊዜ እንኳን በባዶ ቤት ለሃዘን ስፍራ አለመስጠትን አልተማርሽም! የተሰማኝን እኔ ራሴ አውቀዋለሁ። አቅሙ ቢኖረኝ ኖሮ ማዘኔን አሳያቸው ነበር። አጓጉል ሙከራ ሞክሬ ግን ከመቅለጥ

አለመሞከርን እመርጣለሁ። አውቃለሁ እውነት ባንቺ ዘንድ እንጂ በኔ ዘንድ አይደለችም።ሳልታሰር መኖር ከፈለግሁ ጌቶቼን መስማት አለብኝ።

ኤሌክትራ

ከአባታችን ተወልደሽ እናታችንን ብቻ መስማትሽ ጉድ ነው።ደግሞም አሁን ያነበነብሽቸው ሁሉ የእሷ እንጂ ያንቺ ሃሳቦች አይደሉም። አሁን ግን በአንድም ሆነ በሌላ መልክ ውሳኔ ላይ መድረስ አለብሽ።እኔ ለበቀል ርምጃ በወሰድኩ ቁጥር እኔን ከመከላከል ሌላ አታውቂም። እስቲ ንገሪኝ ስለ አባቴ ማልቀሴን ባቆም የምጠቀመው ምንድነው? ኑሮ ነው ከተባለ ይሄው እያዘንኩስ እኖር የለ? በእርግጥ ክፉ ኑሮ እንደሆነ አውቃለሁ። ቢሆንም ግን ይበቃኛል። በወዲያኛው ዓለም ደስታ ካለ እነዚህን እያሳረርኩ ለአባቴ የሃዘን ግብሩን እሰጠዋለሁ።አንቺ ግን በአንደበትሽ ብቻ እንደምትጠያቸው እያወራሽ ከአባትሽ ገዳዮች ጋር ተስማምተሽ ትኖሪያለሽ። አሁን አንቺ አለኝ እያልሽ የምትኮሪበትን ነጻነት ቢሰጡኝ እንኳን እንደምመልስላቸው ነው የምነግርሽ። የበለጸገው ጠረጴዛና የተትረፈረፈው ምግብ እዚያው ላንቺ ይሁንሽ።ለኔ ሚያሻኝ ምግብ የገዛ ህሊናየ ነው። የአንቺ አይነቱን ክብር ለመክበር አልፈልግም። አንቺም የምን ዓይነት አባት ልጅ እንደሆንሽ ባወቅሽ ይህን ዓይነቱን ክብር ባልፈለግሽ እናትሽንም ባልሰማሽ ነበር። ማንም እንደሚያረጋግጠው ከሃዲና የወዳጇ ደመኛ ናት።

ማይሴናዊት

በሁለታችሁም ዘንድ ምንም ቁጣ አያስፈልግም። አንቺ እሷን ብትሰማሽ አንቺም እሷን ብትሰሚያት ነው መልካም።

ክሪስቶሚስ

አንደበቷ እንደሆነ የለመድኩት ነው።ከሃዘንና ለቅሶዋ ለማስቆም እድምዬን ሙሉ ነው የጣርኩት።

ኤሌክትራ

እስቲ ያንቺን ሃዘን ንገሪኝ እኔ ካለሁብት ሃዘን የባሰ ከሆነ ይሄው ለመስማት እምቢ አልልም።

ክሪስቶሚስ

ከሰማሽኝ መልካም ነው እነግርሻለሁ። አሁን የያዝሽውን ለቅሶ የማታቆሚ ከሆነ እድሜ ልክሽን የፀሃይ ብርሃን ወደማታገኚበት ስፍራ ሊያግዙሽ ወስነዋል። ቀሪ

እድሜሽን በዋሻ ውስጥ እንድታሳልፊ ተፈርዶብሻል። ይህነን ስለሰማሁ ነው ላሳስብሽ የመጣሁት። እኔን ባለማዘኔ መውቀስሽን ትተሽ አንቺ ራስሽ ለድርጊትሽ ሃላፊ ሁኚ።

ኤሌክትራ

ይሄንን ሊያደርጉብኝ ነው የወሰኑብኝ።

ክሪስቶሚስ

በትክክል! ኤግስተስ ከሄደበት ሲመለስ።

ኤሌክትራ

እንግዲያውስ ቶሎ በተመለሰ!

ክሪስቶሚስ

ለምን ክፉ ነገር ትመኚያለሽ የኔ ውድ?

ኤሌክትራ

ያለውን ካደረገማ በተቻለኝ ፍጥነት ሁሉ ካንቺ ንትርክ እርቃለሁ።

ክሪስቶሚስ

ለህይወትሽ ምንም ደንታ የለሽም ማለት ነው?

ኤሌክትራ

ምንም የተሻለ ነገር የለም።

ክሪስቶሚስ

ሰዋዊ ባህርይን ከተላመድሽ አለ።

ኤሌክትራ

ለምወዳቸው ሰዎች ክፉ እንድሆን አታስተምሪኝ።

ክሪስቶሚስ

ይሄ የኔ ትምህርት አይደለም። የባለስልጣን ትዕዛዝ ነው።

ኤሌክትራ

አድር ባይነትሽን ቀጥዪ! እኔ ግን ስራዬ አይደለም።

ክሪስቶሚስ

ደደብነት ጥላ ስር አለመውደቅ ግን መልካም ነገር ነው።

ኤሌክትራ

የአባቴን ደም መበቀል ካለብኝ እስከመጨረሻው እታገላለሁ።

ክሪስቶሚስ

አባቴ ይቅር እንደሚለኝ አውቃለሁ።

ኤሌክትራ

ምንጊዜም ቢሆን ወራዳ ሰው የሚለው እንደዚህ ነው።

ክሪስቶሚስ

እና አትሰሚኝም? በሃሳቤ አትስማሚም?

ኤሌክትራ

በፍጹም አልስማማም። በምንም ነገር ፈጽሞ ተስፋ ቢስ አልሆንም።

ክሪስቶሚስ

እንግዲያውስ ወደ ታዘዝኩበት ስፍራ መሄድ አለብኝ።

ኤሌክትራ

ወዴት ነው የምትሄጂው?ለማነው ይሄንን ፈሻስ መስዋዕት የምትወስጅው?

ክሪስቶሚስ

እናቴ ናት ወደ አባቴ መቃብር ስፍራ መስዋዕት እንዳደርስ ያዘዘችኝ።

ኤሌክትራ

ምንድነው የምትይው? ለታላቁ ጠላቷ?

ክሪስቶሚስ

“ለገደለችው ሰው!” የሚለውንም ጨምሪበት።

ኤሌክትራ

የትኛው ወዳጇ ነው የመከራት? የማነኛቸው ሃሳብ ነው?

ክሪስቶሚስ

የሌሊት ሽብር መሰለኝ እንዲህ ለማድረግ ያበቃት።

ኤሌክትራ

የአባቴ አማልክት! ዛሬም ሆነ መቼም ለወዳጆቼ ይቆሙላቸዋል።

ክሪስቶሚስ

እንዴት ነው በሌሊት ህልም እንዲህ የምትተማመኚው?

ኤሌክትራ

ያንን ህልሟ ምን እንደነበረ ስትነግሪኝ እነግርሻለሁ።

ክሪስቶሚስ

ብዙ ልነግርሽ አልችልም። ጥቂት ነገር ብቻ ነው ።

ኤሌክትራ

ያንን ጥቂቱንም ቢሆን ብትነግሪኝ ያው ነው።

ክሪስቶሚስ

እናታችን የኔም ያንቺም አባት ዳግም አብሯት ሊኖር ሲመጣ በህልሟ ሳታይ አልቀረችም። በአንድ ወቅት ይይዝ የነበረውን ዛሬግን ኤግስተስ የያዘውን በትረ መንግስት ጨብጦ አየችው። በትረመንግስቱም ድንገት ለምልሞ አንድ ትልቅ ዛፍ ይሆንና ጥላውን በድፍን ሚሲና ያጠላል። ይህንን ህልሟን ለጸሃይ ስትናዘዝ ነው የሰማት ሰው የነገረኝ። ከዚህ በኋላ ይህንን መስዋዕት ለአባቴ እንዳፈስስ እንደነገረችኝ ነው የማስታውሰው። አንቺ ግን አደራሽን ደግሞ እንደ ልማድሽ አጉል ነገር እንዳታደርጊ። እኔን ካልሰማሽ ወዳንቺ መምጣቷና መቅጣቷ አይቀርም።

ኤሌክትራ

ይሄውልሽ ውድ እህቴ በጠላት ሚቀርብ መስዋዕት በአማልክት ህግ የተፈቀደ አይደለም። ስለዚህ ውሰጅና እዛ ወዲያ ለነፋስ በትኛቸው። አለዚያም ብኛኙ እንኳን

ለአባቴ መቃብር እንዳይደርስ ጥልቅ ስፍራ ጉድጓድ ምሰሽ ቅበሪያቸው። ለሷ የክፉ ቀን ስንቅ ይሁኗት። የክፉዎች ሁሉ ራስ ባትሆን ኖሮ በገዛ እጇ ለገደለችው ሰው ፈሳሽ መስዋዕት ትልክ ነበር?ክብሩንና ነፍሱን በአንድ ምሽት የተነተቀው ሰውስ ቢሆን ይሄንን የሚቀበል ይመስልሻል? አይሆንም! ከራስሽ ጸጉር አንድ ዘለላ ቁረጭና የኔንም ጨምረሽ በምስኪን ልጆቹ በረከት ለአባታችን መስዕት አቅርቢለት። ልጁ ኦሬስቲስ ተመልሶ ለበቀል ይረዳን ዘንድ እንዲልክልንም ተለማመኚው። አየሽ የህልሙ ሰቡብ ይሄ ነው። ምልሽን አድርጊ እህቴ። ለኔ ለእህትሽ ከምንም በላይ ውድ ለሆነው በከርሰ ምድር ለተኛው አባታችን ስትይ ይሄንን አድርጊ።

ማይሴናዊት

ኤሌክትራ መልካም ብላለች። አንቺም መልካም ሰው ከሆንሽ ትቀበያታለሽ።

ክሪስቶሚስ

አደርገዋለሁ። በጎ የሆነውን ነገር ማድረግ ለሁለታችንም ቀላል ነው። አንድ ነገር ለማድረግ መተባበር አለብን። ግን ይሄንን ማድረግ ካለብኝ ወዳጇ ያንቺን ጸጥታ ማግኘት አለብኝ። እናቴ ይሄንን ከሰማች በዚሁ መከራዬ የተነሳ መጥፋቴ ነው።

ማይሴናዊት

የከሰረች ነቢይት ካልሆንኩኝ በቀር የፍትህ ቀን ቀርቧል።በእጁም ድል ጨብጧል። በዚህም እርግጠኛ ነኝ።የህልሙ ሰቡብ ይሄ ነው። የግሪኩ ንጉሥ አባታችሁ ሞቱንም ሆነ የገደለውን መጥረቢያ አልረሳም። የበዙ እጆችና እግሮች በቅርቡ ወደዚህ ለበቀል ይመጣሉ። ባልተፈቀደ አልጋ የተጣመሩ ሁሉ የተረገሙ ናቸው። ምክንያቱም ጋብቻው በሞት ረክሷል። በዚህም ብርሃንነት ክፉ በሰሩት ላይ አንድ ነገር ሳይሰነዝር እንደማይቀር ተረድቻለሁ።ይህን የሚሰሩ ካልተቀጡ በሰዎች ዘንድ ነቢይነት ዋጋ የለውም።

(ክላይቴምኔስትራ ትገባለች)

ክላይቴምኔስትራ

አሁንም ወዲህ ወዲያ እያልሁ በዚህ ቆመሻል?ኤግስተስ እዚህ የለም። ወደ ውጭ ወጥተሽ ቤተሰብሽን ከማዋረድ የሚከለክልሽ ሰው የለም። ስለዚህም የታዘዝሽውን አትሰሚኝም። አንቺንና ያንቺን የሆኑትን ሁሉ እያዋረድሽ በደሌን ታበዢዋለሽ። በኔ ውስጥ ግን አንዲትም በደል የለም። በአንቺ እየተበደልኩ ግን እኔም በአንቺ እበድላለሁ። አባትሽ! አዎ አባትሽ! ለነገሩ ሁሉ መጀመሪያ የአባትሽ በኔ እጅ መሞት

ነው። ይህንን አውቃለሁ። የምክደው ነገር የለም። እውነት ነው። የገደልኩት ግን እኔ ብቻዬን ሳልሆን እውነትም ጭምር ነው። ቀጥጠኛ ሃሳብ ቢኖርሽ የዕውነትን ፍርድ በተቀበልሽ ነበር። ጠዋትና ማታ የምትነፋረቂለት አባትሽ አይደለም እንዴ በእርግዝናና በምጥ ያልደከመባትን ልጇን ለአማልክቱ መስዋዕት አድርጎ ያቀረበው? ንገሪኝ እኪ! ለምንድን ነበር የሰዋት? ለግሪክ ነው ልትይኝ ነው? ግሪካውያን ከኔ ልጅ ሞት ሚያተርፉት ነገር የለም። ለወንድሙ ለሜኔላውስ ሲል ነው የገደላት። እና ለዚህ ተግባሩስ ዋጋ መክፈል የለበትም? ከኔ ልጅ ይልቅ ሁለቱ ሜኔላውስ ሴት ልጆች አልነበሩም መሞት የነበረባቸው? በአባታቸው ጦስ ምክንያት አልነበረም እንዴ ግሪካውያን ሁሉ ወደ ትሮይ የዘመቱት? ወይስ አማልክቱ ከኔ ልጅ ደም የተለየ ነገር አላቸው ልትይኝ ነው? ያ ርጉም አባትሽ ከኔ ልጅ በላይ ለሜኔላውስ ልጆች አላዳላም? ይሄ ታዲያ አእምሮ ማጣት ወይ ክፉ አሳቢነት እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? ምንም አንቺ ከኔ ሃሳብ ብትለይም የኔ ሃሳብ እንደዚህ ነው። ሚቿ ልጄ በህይወት ብትቆይ ኖሮ ከጎኔ እንደምትቆም ጥርጥር የለውም።በሆነው ሁሉ አልጸጸትም። የተረገመች ሴት አድርገሽ ከቆጠርሽኝም እንደፈቀደሽ!

ኤሌክትራ

ይሄ ካንቺ የምቀበለው መከራ ሁሉ በአንድ ወቅት ካንቺ የወረስኩት ጦስ ነው። የምትሰሚኝ ከሆነ እኔም በሚች እህቴና አባቴ ስም የምናገረው አለኝ።

ክላይቴምኔስትራ

በትክክልም እፈቅድልሻለኁ። ንግግራችንን ዘወትር እንዲህ ብትጀምሪው ለመሰማት ባልተሰቃየሽ ነበር።

ኤሌክትራ

እንግዲያውስ እነግርሻለሁ። አባቴን መግደልሽን በገዛ አንደበትሽ ተናዘሻል።ምክንያትሽ እውነትም ይሁን ስህተት ከዚህ የከፋ ምን አሳፋሪ ነገር አለ? አባቴን የገደለሽበት ምክንያት በፍትህ ጥማት ሳይሆን በፍትወት ጥማት ነው። የነፋስ አውታሯን በአውሊስ ገጽ ላይ የጣለችውን አርጤምስን ጠይቂያት። ወይም እሷን ከፈራሻት እኔ ልንገርሽ። አባቴ ወደ ዘመቻ በወጣበት ሰዐት ለአማልክት የተቀደሰችውን እንስሳ ባለማወቅ ገደለ። በዚህም የተነሳ ሌቶ እጅግ አድርጋ ተቆጣች።ስለዚህም አባቴ በገደላት አውሬ ምትክ ሴት ልጁን እህቴን አይፍጂኒያን እስኪሰዋላት ድረስ ግሪኮችን በጦር ወረረቻቸው። የእህቴ መሰዋት ምክንያት ይሄ እንጂ ሌላ አልነበረም። አባቴ እህቴን ሰውቶ የአማልክቱን ፈቃድ ላለመሙላት እጅግ አድርጎ ታገለ። ነገር ግን አልቻለም። በመጨረሻም መስዋዕት አድርጎ አቀረባት። በቃ ታሪኩ ይሄ ነው። አንቺ

እንደምትዬው ለሚኔላውስ ሲል አልገደላትም። ደግሞስ አንቺ እንደምትይው ለወንድሙስ ሲል ቢገድላት እሱ ባንቺ እጅ እንዲሞት ይሄ ሰቡብ መሆን ነበረበት? የትኛው ህግ ነው ይሄን የደነገገው? ወይስ አንቺ ያወጣሽው ህግ ነው? ስለአንዱ ሰው መሞት ሌላው መሞት ካለበት ዋናዋ ሟች አንች መሆን ነው ያለብሽ።እሱን የገደልኩት ልጇን ስለ ገደለብኝ ነው ካልሽ እስቲ በሞቴ ንገሪኝ ከገዳዩ ጋር በፍትወት መጋለብሽስ በምን ምክንያት ነው? ከቀድሞ ባልሽ በተገኘ ክቡር ጋብቻ የተወለዱ ልጆችሽን አባረሽ የውሽማሽን ዲቃሎች መፈልፈልሽስ ምን ሊባል ነው? ለዚህ ርኩስ ተግባርሽስ ምን መሰረት ልጣልለት? ይሄንንም ለልጇ ስል አደረግሁት ልትይኝ ነው? ለልጅሽስ ካዘንሽላት ከአባቷ ገዳይ ጋር ባልተጋባሽ ነበር። እኔ ራሴ ጭራሽ እንደ እናቴ አላይሽም። አሽቆጥቁጣ እንደምትገዛኝ እመቤቴ ነው የምቆጥርሽ። በአንቺና አልጋሽን በሚጋራሽ ርጉም ሰው ምክንያት ዘወትር እንደተሰቃየሁ ነው። ሌላው ወንድሜ ኦሬስቲስ በጊዜ ከወጥመድሽ አምልጦ በባእድ ሃገር በስደት ይባዝናል። ገዳይሽ እንዲሆን እኔ ደብቄ እንዳሳደግሁት አድርገሽ ዘወትር ትረግሚኛለሽ። ደግሞ ላረጋግጥልሽ በተቻለኝ አቅም ሁሉ ይህንን ከማድረግ አልመለስም። ከዚህ የተነሳ ከፈለግሽ ከሃዲ ብለሽ ርገሚኝ።

ማይሴናዊት

ይህንን የምትናገረው በተበሳጨ መንፈስ እንደሆነ አውቃለሁ።እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ ራሴ ምን እንደምል አላውቅም።

ክላይቴምኔስትራ

ለአካለ መጠን ስትበቃ እናቷን እንደዚህ ከምታዋርድ ሴት ቀድሞስ ምን እጠብቃለሁ? እንዲህ ሃፍረተ ቢስ እንደሆነች የትም ምትደርስ እንዳይመስልሽ።

ኤሌክትራ

አንቺ መስሎ ባይታይሽም በምናገርሽ ንግግር እኔም በጣም አፍሬያለሁ።መሆን እንደማይገባኝ እየሆንኩ እንደሆነም አውቃለሁ።ሆኖም ይሄንን ለማድረግ ያበቃኝ አንቺ በኔ ያሳደርሽው ገደብ አልባ ጥላቻ ነው።የክፉ ነገር ሁሉ መነሻው ሌላ ክፉ ነገር ነው።

ክላይቴምኔስትራ

ክፉ! እፍረተ ቢስ ፍጥረት! ገራገሩና ለስላሳው አንደበቴ ነው ለእንደዚህ ያለው ድፍረት ያበቃሽ!

ኤሌክትራ

መጀመሪያውኑ ነገሩን ያነሳሽው እኮ አንቺ ነሽ። ለኔ ክፉ ቃል መነሻውም ያንቸው ክፉ ንግግር ነው።

ክላይቴምኔስትራ

በእመቤቴ አርጤምስ ስም እምላለሁ። የክፋትሽን ውጤት ኤግስተስ ከሄደበት ሲመጣ ታገኚዋለሽ።

ኤሌክትራ

አየሽ! የፈቀድኩትን እንድናገር ከፈቀድሽልኝ በኋላ አንቺው መልሰሽ ታብጃለሽ። ማድመጥ ምን እንደሆነ እንኳን አታውቂም።

ክላይቴምኔስትራ

በይ አሁን አፍሽን ሰብስቢልኝ። የፈቀድሽውን እንድትናገሪ ፈቅጄልሻለሁ። አንቺ ደግሞ በተራሽ ለአማልክት መስዋዕት እንዳቀርብ ተይኝ።

ኤሌክትራ

እተውሻለሁ። ተናግሬ ላላተርፍ ለምን አጉል እደክማለሁ? ያው መስዋዕትሽን አቅርቢ። ከንፈሮቹን አትርገሚ። እኔም እንደፍላጎትሽ ምንም አልናገርም።

ክላይቴምኔስትራ

*(ለአፖሎ ምስል)*

የሙታን ዓለም አማልክት፣ ከአንደበቱ ሳላወጣ ምነግራችሁን እነዚህን ቃላት ስሙኝ። ለናንተ የምነግራችኁ ቃላት ከቶም በአደባባይ ሊነገሩ የማይቻሉ ናቸው። ይልቁንም ይህቺ ልጅ እዚህ አጠገቤ ቆማ ከቶም ልናገረው አልችልም። የህልሜን ጣምራ ፍቺ እነሆ በጆሯችሁ አፈስሳለሁ። አሁን ካለሁበት ጸጋ ሊቀንሱኝ የሚወዱትን ሰዎች አትፍቀዱላቸው። እስካሁን እንደኖርኩ ሁሉ ወደፊትም በአትሪውስ ቤትና ዙፋን በተድላ ከወዳጆቹ ጋር ልኑር። አምላኬ ጸሎቱ ይህ ነው። ጆሮህን ሰጥተህ አድምጠኝ። የጠየቅንህን ስጠን። ከዚህ የተረፈውን የልቤን መሻት አምላክ ነህና አንተ ታውቀዋለህ። የዜውስ ልጆች ሁሉን ማወቃቸው ተፈጥሯዊ ባህርያቸው ነው።

(ፔዳጎጀስ ይገባል)

ፔዳጎጀስ

የተከበራችሁ እመቤቶቼ! የኤጅስተስ ቤተ መንግስት ይሄ ይሆን!

ማይሴናዊት

ግምትህ ትክክል ነው። ቤተ መንግስቱ ይህ ነው።

ፔዳጎጀስ

እንግዲያውስ ይህቺ እመቤት ንግስቲቱ እንደሆነች ብገምት እሳሳት ይሆን? አቋሟ የንጉሳዊ ቤተሰብ ይመስላል።

ማይሴናዊት

በትክክል ራሷ ናት! እነሆ ከፊትህ ቆማለች።

ፔዳጎጀስ

ሰላም ላንቺ ይሁን ግርማዊት! ላንቺ፣ ለኤግስተስና ለመልካም ወዳጆቻችሁ ቸር ወሬ ይዤላችሁ መጥቻለሁ።

ክላይቴምኔስትራ

ያልከውን እቀበላለሁ። አስቀድሞ ግን ወዲህ የላከህን ሰው ማንነት ባውቀው እወዳለሁ።

ፔዳጎጀስ

ፎኔሺያዊው ወዳጃችሁ ፍኖቴዎስ ነው ከታላቅ መልእክት ጋር ወዲህ የላከኝ።

ክላይቴምኔስትራ

ምንድነው ነገሩ ጌታው! እባክህን ንገረኝ። ከወዳጅ ዘንድ ነውና መጣኸው የወዳጅ ዜና እንደያዝህልኝ አውቃለሁ።

ፔዳጎጀስ

ኦሬስቲስ ሞቷል! ይሄው ነው በአንድ አጭር ቃል።

ኤሌክትራ

ወይኔ! ወይኔ አምላኬ! ወይኔ አምላኬ! ይሄ የሞትኩበት ቀን ነው።

ክላይቴምኔስትራ

ምንድነው ያልከው ጌታው! ምንድነው?

ፔዳጎጀስ

ቅድም ያልኩትና አሁንም ቢሆን ደግሜ የምለው ኦሬስቲስ ሞቷል ነው።

ኤሌክትራ

አምላኬ እባክህ እርዳኝ! ሞቻለሁ! ከእንግዲህ መኖር አልችልም።

ክላይቴምኔስትራ

እሷን ለራሷ ተዋት! እንዴት ሆኖ እንደሞተ እውነቱን እስኪ ንገረኝ።

ፔዳጎጀስ

እንድናገር የተላክሁት እውነት ይሄ ነውና እነግራችኋለሁ። ግሪካውያን ሁሉ ወደሚያከብሩት የውድድር ስፍራ ሄደ። በዚያም ከአዋጅ ነጋሪው የመጀመሪያው የውድድር አይነት ሩጫ መሆኑን ሰማ። መወዳደሪያው ሜዳ ሲገባ የሰው ሁሉ ዐይን እሱ ላይ ነበር። ውድድሩ ተጀመረ። ሩጫውም እንደቁመናው ያማረ ነበር። ውድድሩን ፈጽሞ በክብር ወደ መሸለሚያው አደባባይ ወጣ። ሌላም ብዙ የምነግራችሁ ነገር ነበር። ብቻ አሳጥሬ መናገር አለብኝ። እንደዚህ ዓይነት ሰው በእድሜየ ሙሉ አይቼ አላውቅም።የተወዳደረበትን ውድድር ሁሉ በድል ያጠናቀቀ ሰው የማውቀው እሱን ብቻ ነው ያየሁት።በውድድሩም መጨረሻ ላይ አዋጅ ነጋሪው የውድድሩ አሸናፊ አርጊቭዊው የቀድሞው የትሮይ ጄኔራል አጋሜምኖን ልጅ ኦሬስተስ ሚሰኝ ሰው መሆኑን ተናገረ። ብቻ አምላ መቅሰፍቱን ሲያወርድ ብርቱም ሰው ቢሆን ሊያመልጥ አይችልም።በሚቀጥለው ቀን ጀንበር ካዘቀዘቀች በኋላ የሚቀጥለው ውድድር የሰረገላ ሽቅድምድም መሆኑ ተነገረ።ኦሬስተስም ለውድድሩ ተሰለፈ።አንድ ኤቸያዊ፣ አንድ ስፓርታዊ፣ ሁለት ሊብያውያን ሆነው ለውድድር ተሰለፉ። ኦሬስቲስ ከነሱ ጋር አምስተኛ ሆኖ ተቆጠረ።ስድስተኛው ኢቶልያዊ፣ ሰባተኛው ሰባጠኛው ኤንያዊ፣ ስምንተኛው አቴናዊ፣ ዘጠነኛው ቦዬሺያዊ ሆነው በጋራ ለውድድር ተሰለፉ።ሁሉም ዳኛው በወሰነላቸው ቦታ ተደረደሩ። በመጨረሻም የውድድሩ ማብሰሪያ ጥሩምባ ተሰማና ውድድሩ ተጀመረ። ሁሉም ፈረሶቻቸውን እያጣደፉ ሰገሩ።በኋላ ግን

የሰረገላዎቻቸው ጋሪዎች እርስ በእርሳቸው መጋጨት ጀመሩ። ይህን ጊዜ አቴናዊው ተወዳዳሪ አፈተለከና ወጣ። ኦሬስተስ ዓላማውን ሁሉ ከውድድሩ ፍጻሜ ላይ አድርጎ ከኋላ ነበር የሚጋልበው። ሆኖም የአቴናዊውን ማፈትለክ ሲያይ እሱም ፈጥኖ ጋለበና ደረሰበት።አንዴ አንዱ አንዴ ሌላው እያሉ የሞት ሽረታቸውን ተወዳደሩ። ኦሬስተስ በውድድሩ ሜዳ አጥር ጥግ ነበር የሚጋልበው። በመጨረሻ ፈረሱ ሲዞር አጉል ተጠመዘዘና መሃሉ ላይ ተሰበረ። ኦሬስቲስ ከሰረገላው ተፈናጠረና መሬቱ ላይ ተፈጠፈጠ። ገና ከመከስከሱ ከኋላው የነበሩት ፈረሶች ሲጋልቡ በመጡበት ፍጥነት እየደቀደቁት አለፉ።ሲወድቅ ያዩት ሰዎች ሁሉ "አዬ ጉድ! እንዴት ያለ ወጣት ነበር!" "እንዴት ያለው ሳተና ጉድ ሆነ!" "አዬ ሲያልቅ አያምር!" እያሉ አንጎራጎሩ። ኦሬስተስም በደም ተጨማልቆ ሚወደው ሰው እንኳ ቢያየው ሊለየው አይችልም ነበር። ወዲያውም  አስከሬኑ በክብር እንዲቃጠል ተደርጎ ከሰዎች መካከል ፎኔሽ'ያዊው ወዳጃችሁ ተመረጠና የበድኑን አመድ በነሃስ ሳጥን አድርጎ ወደ አባቱ ሃገር እንዲያደርሰው ተወሰነ። እንግዲህ ለኛ ለተመከትነው እጅግ አሳዛኝ የሆነው ወሬ ይሄ ነው።

ማይሴናዊት

ውይ! ውይ! የሃገራችን ቀዳሚ ነገድ  ስርና ቅርንጫፉን እንኳ ሳይተው ተቀጠፈ!

ክላይቴምኔስትራ

ዜውስ! ምንድነው ማለት ያለብኝ! "መልካም እድል" ልበል ወይስ "ለክፉ የሆነ መልካም እድል"? ለራሴ የምሆነው ሁሉ መላ ቅጡሱ ጠፋኝ።

ፔዳጎጀስ

የኔ እመቤት ለምን ይሆን ይሄ ታሪክ የረበሸሽ?

ክላይቴምኔስትራ

እናትና ልጅ! የሚያስደንቅ ተዛምዶ ነው። ምንም በልጇ ብትጎዳም አንዲት እናት ልጇን ከቶ ልትጠላ አትችልም።

ፔዳጎጀስ

እንግዲያውስ የኔ ወዲህ መምጣት ምንም ዋጋ የለው ማለት ነው።

ክላይቴምኔስትራ

የለም! ጥቅም አልባማ አይደለም። እንዴት ጥቅም አልባ ነው ትላለህ? የመሞቱን መገለጫ ይዘህ እስከመጣህ ድረስ መምጣትህ ጥቅም ያለው ነው። በቀንም ሆነ በሌሊት ረፍት የሚባል ነገር የለኝም። ጊዜ ግን ነገሩን በሞት እልባት ሰጠው። በሱና በሷ ፍርሃት ተጠምጄ ስኖር ነበር። አሁን ግን ነጻ ወጥቻለሁ። እጅግ ታላቅ ጠላቴ ናት። በገዛ ቤቴ እየኖረች ስታስፈራራኝ ኖራለች። አሁን ከዚህ ሁሉ ነጻ ነኝ። የቀኑ ብርሃን ዳግም ተመልሶ ይመጣል።

ኤሌክትራ

አምላኬ! አምላኬ! ኦሬስቲስ አሁን ላንተ ላልቅስልህ። እናትህ እዚህ ቆማ የስድብ መዓት ስታዘንብብህ። ይሄ ትክክል ይሆናል?

ክላይሜኔስትራ

ላንቺ ትክክል አይደለም። ለሱ ግን ትክክል ሆኗል።

ኤሌክትራ

የሙታን አምላክ ኔምሲስ! ይሄንን ጉድ ትሰሚያለሽ?

ክላይሜኔስትራ

ሰምታለች። የእውነት ፍርድም ፈርዳለች።

ኤሌክትራ

እንግዲህማ ዕድል ያንቺ ነው። እንደፈቀደሽ ስደቢተኝ።

ክላይሜኔስትራ

አንቺም ሆንሽ ወንድምሽ ኦሬስቲስ ይሄንን ነገር አትተዉም?

ኤሌክትራ

በትክክልም ትተናል። ልናስቆምሽ አንችልም።

ክላይቴምኔስትራ

/ለመልእክተኛው/

ይህቺን ልጅ ካስቆምክልኝ መምጣትህ በትክክልም ዋጋ ያለው ይሆናል።

ፔዳጎጀስ

የመጣሁበትን ከፈጸምሁ እንግዲህ እኔ ልሂድ።

ክላይቴምኔስትራ

የለም የለም! በፍጹም እንዲህ አይሆንም። ለኔም ሆነ ወዲህ ለላኩህ ወዳጆቼ አንተን በባዶ መመለስ የተገባ ስራ አይደለም። እሷን ለግድግዳዎቿና ለወዳጆቿ ተዋትና አንተ ወደ ውስጥ ግባ።

/ክላይቴምኔስትራና ፔዳጎጀስ ወደ ውስጥ ይገባሉ።/

ኤሌክትራ

እንዴት ያለች ክፉ እናት ናት! እንዴት እንደምትቀናቀንህ ተመልከት። አምላኬ! እየሳቀችኮ ተለየችኝ። ኦሬስተስ የኔ ውድ! ያንተ ሞት ለኔም ሞቴ ነው። መሞትህ አንድ ቀን ወዲህ መጥተህ የአባቴን ሞት ትበቀላለህ የሚለውን ተስፋዬን ነው ያጨለመው። አሁን ወዴት ነው የምደርሰው? አንተንም አባቴንም ነው የተነጠቅሁት። እጅግ ለምጠላቸው የአባቴ ገዳዮች ዳግም ባሪያ መሆኔ ነው። ይሄ ነው ለኔ የሚገባው? ይሄንን በፍጹም አላደርግም።ራሴን እሰውራለሁ። የኔ ባለውለታ ሞት ነው።ለተቀናቃኝ ህይወት ምንም ፍላጎት የለኝም።

ማይሴናዊት

አረ የዚዩስ መባርቅት ወዴት ናቸው!? ጸሃይስ ፍርዷ ወዴት ነው? ይህንን እየተመለከቱ እንዴት ዝምታን ወደዱ?

ኤሌክትራ

ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ!

ማይሴናዊት

ለምን ታለቅሻለሽ የኔ ወዳጅ?

ኤሌክትራ

ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ!

ማይሴናዊት

ኧረ በበለስ ዝም በይ!

ኤሌክትራ

አጥፊየ ነሽ ነው የምልሽ!

ማይሴናዊት

እንዴት እንዴት! እኔ? ምን በደል በበደልኩሽ?

ኤሌክትራ

ዓለም እንዲህ ጨለሞብኝ ልታጽናኚኝ ከሞከርሽ ከሁሉ የከፋሽ አጥፊዬ አንቺ ነሽ።

ማይሴናዊት

ለምን እንዲህ ታመሪያለሽ የኔ ወዳጅ? ንጉሥ አምፊያንስም እንዲሁ በሴት ወጥመድ ወድቆ ነበር።ዛሬ ግን ከአፈር በታች ነው ያለው።

ኤሌክትራ

ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ!

ማይሴናዊት

አዎን ወየው የሚያሰኝ ነው።

ኤሌክትራ

እውነት ኦሬስቲስ ሞተ?

ማይሴናዊት

አዎን ሞተ!

ኤሌክትራ

እሱ ከስቃይ ተገላገለ።

ማይሴናዊት

አወይ አለመታደል! ያለመታደል ራስ ነሽ!

ኤሌክትራ

ለሆነው ሁሉ ምስክሬ አንቺ ነሽ! ልታስቆሚኝ አትሞክሪ!

ማይሴናዊት

የምትይውን አውቃለሁ።

ኤሌክትራ

እንግዲያውስ አደራሽን ሃሳቤን ለመመለስ እንዳትሞክሪ!

ማይሴናዊት

ምን ማለትሽ የኔ ወዳጅ?

ኤሌክትራ

ከእንግዲህ ወዲያ ለወዳጅ ምንም የቀረ ተስፋ የለም።

ማይሴናዊት

ሞት ለሰው ልጅ ተራ ነው። ሁሉም የሚወለደው ሊሞት ነው። ሞት ከመጣ ማንም ሊያመልጠው አይችልም።

/ክሪስቶሚስ ትገባለች/

ክሪስቶሚስ

የኔ ውድ! ኤሌክትራ እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል። መሮጥ ከሚገባኝ በላይ ነው ስሮጥ ወዲህ የመጣሁት። ስትሰቃይበት ለነበረው መከራ መገላገያ ነው ያመጣሁልሽ።

ኤሌክትራ

ምንም መድህን ለሌለው መከራዬ መድሃኒት የምታመጭልኝ ለመሆኑ አንቺ ማነሽ? ከየትስ ነው መድሃኒት የምታመጭልኝ?

ክሪስቶሚስ

ኦሬስቲስ በመሃላችን አለ። አሁን አንች እንዳለሽው አለ። ይሄንን ዜና ነው ይዤልሽ የመጣሁት።

ኤሌክትራ

አብደሻል ልበል አንቺ ልጅ? ወይስ በገዛ መከራችን ታሾፊያለሽ?

ክሪስቶሚስ

በሚቴ አባታችን አጥንት እምልልሻለሁ። እየቀለድኩኝ አይደለም።ኦሬስቲስ እዚህ በአካል ከኛ ጋራ ነው።

ኤልክትራ

ምስኪን! ማነው እንዲህ እስከታምኚው ድረስ አሳምኖ ነገረሽ?

ክሪስቶሚስ

ስላየሁት ነገር ምስክሮቹ የገዛ ዐይኖቼ እንጂ ሌላ ሰው አይደለም።

ኤሌክትራ

ያልታደልሽ! ያልታደልሽ! ለመሆኑ አየሁት ለምትይው ነገር ምን ማረጋገጫ ነው ያለሽ?

ክሪስቶሚስ

በአምላክ ስም ልለምንሽ! የምነግርሽን ስሚኝ። ከሰማሽኝ በኋላ ከፈለግሽ እብድ ከፈለግሽ ሞኝ በይኝ።

ኤሌክትራ

ታሪኩ ካስደሰተሽ ንገሪኝ።

ክሪስቶሚስ

አዎን ያየሁትን ነግርሻለሁ። ወደ አባቴ መቃብር ስደርስ መቃብር ቦታው ከመግቢያው እስከ ቀብሩ ቦታ ድረስ የነተበ የወተት ፈሳሽ አየሁ። በመቃብሩም ዙሪያ የአበባ ጉንጉን ነበር።ይሄንን ሳይ ምናልባት አጠገቤ ሰው ይኖር ይሆን ብዬ ዙሪያዬን ቃኘሁ። ምንም ነገር እንደሌለ ሳረጋግጥ በቀጥታ ወደ ቀብሩ ሄድሁ። መቃብሩ ላይ ከራስ የተቆረጠ ዘለላ ጸጉር ነበር። ይሄንን ሳይ አንድ ነገር በቤተሰባዊ ስሜት ውስጤ ዘለለ። ያጸጉር የወንድሜ የኦሬስቲስ መሆኑ ገባኝ። አንዳች ነገር ሳልናገር ጸጉሩን አንስቼ አየሁት። አይኔ በእንባ ረጠበ። ይሄ መስዋዕተ ሊሰዋ የሚችለው ከሱ እንደሆነ ገባኝ። እኔ አላደረግሁትም። አንችም እንኳን ለመስዋዕት ለጸሎት እንኳን ከቤት አትወጭም።

ይሄንን ካደረግሽ ትቀጫለሽ። ታዲያ ምን ይሄንን ማን ሊያደርገው ይችላል? እናታችንም ይሄን ልታደርግ አትችልም። እንዲህ ዓይነት ነገር አታደርግም። ብታደርግም ምስጢር አድርጋ አትይዘውም። ይሄን መስዋዕት ያቀረበው ኦሬስቲስ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው።ልብ ብለሽ አስተውዪ የኔ ውድ። እስካሁን እሱ በኛ ዘንድ የተጠላ ነበር። አሁን ግን በአማልክት ኪዳን ዳግም ወደኛ ተመልሷል።

ኤሌክትራ

ጅልነትሽ እንዴት አንጀቴን እንደሚበላው አታውቂም።

ክሪስቶሚስ

ምንድነው እሱ የምትዪው? የምትወጂውን ዜና አይደለም እንዴ ያመጣሁልሽ?

ኤሌክትራ

አንቺም ሆንሽ ሃሳቦችሽ የት እንዳላችሁ አታውቂም።

ክሪስቶሚስ

ምን ማለትሽ ነው? ስላየሽው ነገር ምንም አታውቂም እያልሽኝ ነው?

ኤሌክትራ

ኦሬስተስ ሞቷል የኔ ውድ። አንቺም በሱ ላይ ያለሽ ተስፋ ከሱ ጋር አብሮ ሞቷል። ከእንግዲህ እሱን አትጠብቂው።

ክሪስቶሚስ

ምን! ከማነው ይሄንን ወሬ የሰማሽው?

ኤሌክትራ

በሞተበት ሰዓት አጠገቡ ከነበረ ሰው።

ክሪስቶሚስ

እንግዲያውስ አሁን የታል?

ኤሌክትራ

ቤት ውስጥ! የእናታችን የክብር እንግዳ ሆኖ እየተስተናገደ ይገኛል።

ክሪስቶሚስ

ወይኔ! ታዲያ ማነው ያንን መስዋዕት ቀብሩ ላይ ያስቀመጠው?

ኤሌክትራ

ምናልባት ለሚቹ ኦሬስቲስ መታሰቢያ አንድ ሰው አስቀምጦት ይሆናል።

ክሪስቶሚስ

ወይኔ ያልታደልኩት!! የወደቀብንን መዓት ሳላውቅ እንዴት ነበር መልካም ዜና ለመናገር የሮጥኩት? አሁን ስመጣ ግን ነበሩ ሰቆቃችን አድስ ሰቀቀን ወልዶ ጠበቀኝ!!

ኤሌክትራ

እሱ አንቺ ያየሽበት ነው። አሁን ግን እኔን አድምጭኝ። እናም የተጫነሽን ሰቀቀን አራግፊ።

ክሪስቶሚስ

እንዴት? ሚቹን ዳግም ወደ ህይወት ላመጣው እችላለሁ?

ኤሌክትራ

እንደሱ አይደለም ያልኩሽ። እስከዚህ ሞኝ አይደለኁም።

ክሪስቶሚስ

እንግዲያው እኔ ምችለው አንቺ የምታዥኝ ምንድነው?

ኤሌክትራ

ምክሬን ለመስማት ብርታት እንዲኖርሽ ነው የምመክርሽ

ክሪስቶሚስ

የምረዳው ነገር ካለ በፍጹም እምቢ አልልም።

ኤሌክትራ

ተመልከች! ያለ ብርታት ስኬት የለም።

ክሪስቶሚስ

ይገባኛል! ብርታቴ የፈቀደውን ያህል ልረዳሽም ዝግጁ ነኝ።

ኤሌክትራ

ያቀድኩትን እነግርሻለሁ። ልብ ብለሽ ብቻ አጫውቺኝ። አሁን ሊረዳን የሚችል ወዳጅም ሆነ ዘመድ እንደሌለን እኔ የማውቀውን ያህል ታውቂያለሽ። ሞት ሁሉንም ነጥቆናል። እኔና አንቺ ብቻ ነን የቀረነው። እኔ ግን አሁንም ወንድማችንበህይወት እንዳለና ዳግም የአባታችንን ገዳዮች ሊበቀል እንደሚመጣ ነው የሚሰማኝ። አሁን ግን እሱ ፈጽሞ የለም። አንቺ ግን የእናቴ ልጅ አባታችንን የገደለውን ኤጅስተስን በመግደል እርጂኝ። ሌላ ካንቺ የምማከረው ነገር የለም። እና ምነው አመነታሽ? እንዲህ አድርቆ የሚያስቀር የምን ተስፋ ነው የቀረሽ? አሁን የአባታችን ጥቃት ሊጎፈንንሽ ይገባል። ባል ሳታገቢ ምን ያህል ጊዜ እንዳለፈሽ አስተውዪ። አሁንም አግብቼ እወልዳለሁ ብለሽ ተስፋ አታድርጊ። የሚበቀሉት ልጆች እንድትወልጅ የሚፈቅድልሽ ኤጅስተስ ሞኝ አይምሰልሽ! አሁን ግን ምመክርሽን ከሰማሽ በመጀመሪያ ለሞተው አባትሽና ወንድምሽ ማዘንሽን በተግባር ታረጋግጫለሽ። በኁለተኛ ደረጃ ነጻ ሆነሽ አንደተወለድሽ ነጻ ሆነሽ ትዳር ይዘሽ ለመኖር ትችያለሽ። ይሄንን በማድረግሽ በሃገር ዜጎችና በመጻተኞች ዘንድ የምናተርፈው ዝና አይታይሽም? የሚያውቁንና ዝናችንን የሰሙት ሁሉ “ ተመልከቷቸው እነዚህንን እህትማማቾችና የተዋደዱ ወዳጆች! በላያቸው ና በቤታቸው አንፈራጠው የነበሩትን ጠላቶቻቸውን ለህይወታቸው ሳይሰጉኮ ነው የተበቀሉት! ስለዚህም ጀግንነታቸው ልንወዳቸውና ልናከብራቸው ይገባል!” ሲሉን አይታይሽም? ይሄንን በማድረጋችን ሁሉም የሚለን ይሄንን ነው። በሞትም በህይወትም የማይሞት ዝናን እናተርፋለን። የኔ ውድ አዳምጭኝ። ለአባትሽና ለወንድምሽ አድዪ! ከስቃዬ ገላግዪኝ። ይሄንን አውቀሽ ራስሽንም ገላግዪ።

ማይሴናዊት

በእንደዚህ ያለው ሰዓት አንዳችሁ የሌላችሁን ምክር ተጠንቅቆ መስማቱ ነው የሚበጃችሁ።

ክሪስቶሚስ

የኔ እመቤት! ከመናገሯ በፊት መልካም ሃሳብ ካላት የምትለውን ማድረግ መቻሏን መመዘን ነበረባት።

/ለኤሌክትራ/

ለመሆኑ ያሰብሽውንና እኔም እንድረዳሽ የጠየቅሽኝን ነገር በቁም ነገር ታውቂያለሽ? ማስተዋል አቃተሽ ልበል? ሴት እንጂ ወንድ እኮ አይደለሽም። የአካ ጥንካሬሽ ከጠላቶችሽ ያንሳል እንጂ አይበልጥም። እኛ እየተቀበርን ስንመጣ እነሱ ዕየበለጸጉ ነው የሚሄዱት። ኤግስተስን የሚያህል ሰው ላይ ተንኮልሽርቦ መሳይጎዳ የሚተርፍ ሰው ማነው? በመከራ ውስጥኮ ነው ያለነው። የምትናገሪውን እንኳን የሰማሽ ሰው ድንገት ቢኖር የሚደርሰውን አታውቂም? አጓጉል ነገር ሞክረን የውርደት ሞት ከምንሞት ቢቀርብን ነው የሚሻል። የቤተሰባችንን ብቸኛ ቀሪ ዘሮች አጉል ነገር ሞክረሽ ለዘር እንኳን ሳንተርፍ እንዳታስጨርሺን እለምንሻለሁ። ለኔ የነገርሽኝ ሁሉ ለማንም አይነገርም። ወደ ስሜትሽ ተመለሽ።

ማይሴናዊት

የምትልሽን ስሚያት። በረጋ መንፈስ ከማሰብ የተሻለ ትርፍ ለሰው ልጅ የለም።

ኤሌክትራ

ምንም ያልተጠበቀ ነገር አልተናገርሽም። እቅዴን ሁሉ እንደምትጥይው አውቄዋለሁ። ድርጊቱ በኔ እጅ ብቻ መደረግ አለበት። ምክንያቱም ሳልፈጽመው አልቀርም።

ክሪስቶሚስ

ወይኔ! አባታችንም ሲሞት ይሄ እንደተሰማሽ አውቃለኑ። ይሄንን ሁሉ ከሞተ ጊዜ ደግሞ ስትዪው አውቃለሁ።

ኤሌክትራ

ምንጊዜም ቢሆን በተፈጥሮ እንደዚህ ነኝ። በውሳኔ ግን ደካማ።

ክሪስቶሚስ

ያንን ውሳኔ ለመወሰን በተግባር ሞክሪ

ኤሌክትራ

ይሄም ምክር አንቺ እንደማትረጂኝ የሚያሳይ ነው።

ክሪስቶሚስ

በትክክል! ምክንያቱም ማሰቡ ብቻ ሞትን ያስከትላል።

ኤሌክትራ

ውሳኔሽ ከፍርሃት የመነጨ ነውና እጸረርሻለሁ።

ክሪስቶሚስ

ስትወቅሺኝ እንደነበረው ስታመሰግኚኝም ለመስማት እኩል እታገሳለሁ።

ኤሌክትራ

ይሄንን መቼም ቢሆን ከኔ አታገኚውም።

ክሪስቶሚስ

ይሄንን ለመወሰን ገና ብዙ ወደፊቶች አሉን

ኤሌክትራ

ቀጥይ! ካንቺ የምጠብቀው ምንም ነገር የለም።

ክሪስቶሚስ

እሱስ ነበር! አንቺ ግን ለመማር ፈቃደኛ አይደለሽም።

ኤሌክትራ

ሂጂና ይሄንን ሁሉ ለእናትሽ ንገሪያት።

ክሪስቶሚስ

እንደዚህ ያለ ከሃዲነት በኔ ሃሳብ ውስጥ የለም።

ኤልክትራ

ይሄን ማለትሽ በራሱ ለኔ ውርደት እንደሆነ እወቂ።

ክሪስቶሚስ

ማዋረድ ሳይሆን አርቆ ማሰብ ነው።

ኤሌክትራ

እናም ያንቺን የእውነት ፍርድ መከተል ሊኖርብኝ ነው?

ክሪስቶሚስ

ይሄንን ወደ ስሜትሽ ስትመለሺ ትረጂዋለሽ።

ኤሌክትራ

መልካም በመናገር እውነተኛ አለመሆን ይገርማል።

ክሪስቶሚስ

በትክክል አንቺን የሚመጥን አባባል ነው።

ኤሌክትራ

ምን! ማድረግ ያለብኝን እንደምናገር አትረጂውም።

ክሪስቶሚስ

ቅን ፍርድ ራሱ ጉዳት የሚያመጣበት ጊዜ አለ።

ኤሌክትራ

እነዚህ አብሬ ልኖርባቸው የማልፈቅዳቸው ህጎች ናቸው።

ክሪስቶሚስ

ሙከራሽን ካደረግሽው ያን ጊዜ እኔ ልክ እንደነበርኩ ታውቂያለሽ።

ኤሌክትራ

አዎን አደርገዋለኊ! ልታስቆሚኝ አትችይም።

ክሪስቶሚስ

እርግጠኛ ነሽ? ዳግም አታስቢበትም?

ኤሌክትራ

ከክፉ ምክር የከፋ ምንም ዓይነት ጠላት የለም።

ክሪስቶሚስ

አሁን ካልኩት ነገር በአንዱም እንኳን አትስማሚም?

ኤሌክትራ

ሃሳቤን አሳክቻለሁ። እንደ ትናንት ወላዋይ አይደለሁም።

ክሪስቶሚስ

እንግዲያውስ እሄድልሻለሁ። ቃሌን መቀበል ልትወጂ አትችዪም።

ኤሌክትራ

ሂጂ! እኔም አንቺ እንኳን ብትፈልጊ ዳግም አልጠራሽም።

ክሪስቶሚስ

ጥሩ እንግዲያውስ እሄዳለሁ! ሃሳብሽ መልካም መስሎ ከታየሽ መቀጠል ትችያለሽ። መከራ ውስጥ ስትገቢ ምናልባት ባልኩት ትስማሚ ይሆናል።

ማይሴናዊት

ለወለዷቸው ሃሳብ ይዟቸው በሰማይ የሚበሩ አእዋፍን እናያለን። ለምን ታዲያ እዳችንን አንወጣም። በባለመብረቅ ዝናሩ ዚዩስ፣ በሰማይ ኗሪዋ ቴሚስ ሳይቀጡ ምንም ያህል አይኖሩም። አንተ ወደ መቀመቅ የምትሄድ ድምጽ የሃዘናችንን ብዛት በሞት ለተያዙት አድርስ።ሁለቱ እህታማቾች መጣላታቸውን መቼም ተስማምተው መኖር አለመቻላቸውን ለቤቶቻቸው ንገር። ኤሌክትራ የአባቷን ገዳዮች ለመበቀል ደሟ ሲፍለቀለቅ ሞት ሚባለውን ነገር ፈጽማ ረስታለች።ሁለቱን የአባቷን ገዳዮች ከተበቀለች ብርሃንን ሚባል ነገር ላለማየት ቆርጣለች።ምስኪን ልጅ አሁን እንዳለው ሁሉ ሃይልሽ ከቤተሰቦችሽ በታች ነው።

/ኦሬስቲስ ራሱን ቀይሮ ይገባል።/

ኦሬስቲስ

እመቤቶች! መድረስ ወደ ፈለግንበት ቦታ መድረሳችንን ልትነግሩን ትወዳላችሁ?

ማይሴናዊት

ምንድነው እሱ የምትፈልገው? እዚህስ ምንድነው የምትሻው?

ኦሬስቲስ

በመንገዴ ሁሉ ኤጅስተስ የሚኖርበትን እየጠየቅሁ ነበር የመጣሁት።

ማይሴናዊት

እንግዲያውስ ደርሰህበታል። መንገድ የጠቆመህን መውቀስ የለብህም።

ኦሬስቲስ

እንግዲያውስ ያለሁበትን ስፍራ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ። ከቤተሰቦቹ ልታገኛኙኝ አትችሉም።

ማይሴናዊት

እዚህ እፊትህ የቆመችው ሴት መልዕክትህን ታደርሳለች።

ኦሬስቲስ

እንግዲያውስ እመቤቴ የፎኔቨርያ ሰው እዚህ እንደቆመ ልትነግሪልኝ ትችያለሽ?

ኤሌክትራ

ወይኔ አምላኬ! ይሄ ሰው የእውነታውን ማረጋገጫ ይሆን ያመጣው? በፊት የሰማነውን ጉርምርምታ ማረጋገጫ ይሆን ያመጣኸው?

ኦሬስቲስ

ስለ ጉርምርምታው አላውቅም።ሽማግሌው ስትሮፊስ ነው ስለ ኦሬስቲስ መልዕክት እንዳደርስ የላከኝ።

ኤልክትራ

ምንድነው መልዕክቱ ጌታው። ፍርሃት ነፍሴ ወጥሯታል።

ኦሬስቲስ

በዚህ በምትመለከችው የነሃስ ሳጥን ውስጥ የሱን እስከሬን አመድ ይዣለሁ።

ኤሌክትራ

ወይኔ! ወይኔ! በቃ ይሄ መጨረሻው ነው።ይሄውና መከራዬ ግልጽ አለ።

ኦሬስቲስ

የሱ ሞት እንዲህ የሚጎዳሽ ከሆነ እነሁ የበድኑን አመድ አምጥቼልሻለሁ።

ኤሌክትራ

ጌታዬ! ስለ አማልክት ብለህ ስጠኝ። በሱ ውስጥ ያው የኦሬስቲስ በድን አመድ ከሆነ ስጠኝና በጉልበቴ ተንበርክኬ ስለኔና ስለዘር አዝዕርቴ ላልቅስለት።

ኦሬስቲስ

እንግዲህ ማንም ሁኚ ማን እነሆ በድኑን እሰጥሻለሁ። አነጋገርሽ ከወዳጅ የወጣ ነው የሚመስለው ምናልባትም የደም ቅጂው የሆንሽ ዘመዱ ሳትሆኝ አልቀረሽም።

ኤሌክትራ

በዓለም ላይ ቀርተኸኝ የነበርከው ብቸኛው ፍቅሬ ኦሬስቲስ ያኔ ከዚህ ቤት አስወጥቼ ከሰደድኩህ አቋምህ እንዴት ተቀይረህ መጣህብኝ? ተስፋ ካደረግሁት እንዴት ተለውጠህ መጣህልኝ? ያኔ ስልክህኮ ታላቅ ብልሃተኛ ነበርክ። አሁን በእጄ የያዝኩት ግን ባዶነትን ነው። ያኔ ከሞት ስታደግህ እና ከሞት ሳድንህ እውነት እንደዚህ ነበርክ? ለዚህ ከሆነማ ኖሮ ምናለ ያኔውን ሞተህ በኣባታችን መቃብር ባረፍህ! አሁን ግን ከቤትህ እና ከእህትህ ርቀህ በባዕድ ሃገር በስደት አዘንተኛ ሆንህ ሞትህ። ብድንህን እንኳን ለሙታን በሚገባ ስርዓት አላበጀሁትም። የባእድ ሃገር ሰው ነው እንደ መጻተኛ ያገነዘህ። እናም እጅግ መንምነህ መጣህብኝ። ወይኔ ይሄን ሁሉ መከራ የምቀበልበት የልጅነቴ ልፋት ሁሉ ከንቱ ቀረ። በዚህ ቤት አንድም ወዳጅ አልነበረህም። እኔን ብቻ ነበር “እህቴ” ብለህ የምትጠራኝ። አሁን ግን በአንድ ቀን ያሁሉ ነገር ቀረ። አባታችን ሞቷል። እኔም ባንተ ውስጥ ሞቻለሁ። አንተም ራስህ ሞተሃል። ጠላቶቻችን እንግዲህ ይፈንድቁ። ከእጇ ያዳንሁህ እናትህም ድልን ተቀዳጅተዋል። በኃኃሁለት አቋምህ ፈንታ እነሆ አመድህ መጣልኝ። ወይኔ! ወይኔ!

ማይሴናዊት

አባትሽ ሟች እንደሆነ ሁሉ ኦሬስተስም እንደሚሞት አስቢ እንጂ ኤሌክትራ! እጅግም አብዝተሽ አትሳቀቂ። ይሄ ሁላችንም ልንከፍለው የሚገባ እዳ ነው።

ኦሬስቲስ

ወይኔ! ምንድነው ማለት ያለብኝ? ምን ዓይነት ቃላት ነው መጠቀም ያለብኝ? ከእንግዲህ ምንም የአንደበቴ ባለቤት አይደለሁም።

ኤሌክትራ

አንተን ደግሞ ምን አሳቀቀህ? የዚህ ንግግር ፍቺው ምንድነው?

ኦሬስቲስ

ይህች የተለየችው ውበት ኤሌክትራ አይደለችም?

ኤሌክትራ

አዎ! እስኪበቃት ድረስ በእውነት እየተሰቃየች ያለችው ኤሌክትራ ናት።

ኦሬስቲስ

ወዮ ለዚህ አሰቃቂ ሃዘን!

ኤሌክትራ

ለኔ ብለህ ነው ጌታዬ እንደዚህ የምታለቅሰው?

ኦሬስቲስ

እጅግ በጭካኔ ተበድለሻል!

ኤሌክትራ

እነዚህ ቃላትህ ለኔ ከማዘን ውጭ የተነገሩ ሊሆኑ አይችሉም።

ኦሬስቲስ

ወዮ! ያለ ትዳርና ደስታ ላለፈብሽ እድሜሽ!

ኤሌክትራ

ለምን እንዲህ ታየኛለህ ጌታዬ? ለምን ታዝንልኛለህ?

ኦሬስቲስ

የኔ መከራ ካንቺ አንጻር እንዴት የከፋ ነበር!

ኤሌክትራ

እንዴት ነው እንዲህ ለማለት የበቃኸው?

ኦሬስቲስ

እጅግ አብዝተሽ እንደተሰቃየሁ ነው ያየሁት።

ኤሌክትራ

አሁን አንተ ያየኸው እጅግ ትንሹን የመከራዬን ክፍል ነው።

ኦሬስቲስ

አሁን ከማየው የከፋ ምን አይነት ስቃይ ሊኖር ይችላል?

ኤሌክትራ

ምክንያቱም ከገደሉት ጋር ነው ምኖረው።

ኦሬስቲስ

ምንድነው ያልሽው? የገደሉት እነማናቸው ገዳዮች? ማነው ወንጀልን የሰራው?

ኤሌክትራ

አባቴን የገደሉት። በሃይል የምገዛ ባሪያቸው ነኝ።

ኦሬስቲስ

ማነው እንዲህ እንድትሆኝ ያጋዘሽ?

ኤሌክትራ

እናቴ ናት የምትባለው። እናትነቷ ግን ለምንም ነው።

ኦሬስቲስ

እንዴት ትጫንሻለች? እንዴት ትጻረርሻለች?

ኤሌክትራ

በተቻላት አቅምና ችግር ሁሉ ታስቸግረኛለች።

ኦሬስቲስ

አንቺን የሚረዳሽና እሷንስ የሚያስቆማት ማንም የለሽም?

ኤሌክትራ

የለም። እርግጥ አንድ ነበረ። አሁን ግን አመዱን አሳያችሁኝ።

ኦሬስቲስ

ምስኪን ልጅ! ሳይሽ እንዴት አዘንኩልሽ?

ኤሌክትራ

እንግዲያውስ ብቸኛው ያዘነልኝ ሰው አንተ ነህ።

ኦሬስቲስ

አዎን እኔ ብቻ ወዲህ መጥቼ ህመምሽ ተሰማኝ።

ኤሌክትራ

እንደዘመድ ሆነህ መቼም ወዲህ አልመጣህም

ኦሬስቲስ

እሱን እንግዲህ በሷ ፊት መናገር ካለብኝ እነግርሻለሁ።

ኤልክትራ

አዎን ወዳጇ ናት። በነጻነት ማውራት ትችላለህ።

ኦሬስቲስ

እሱን ሳጥን ወዲያ ጣይና እንግዲያውስ ትሰሚያለሽ።

ኤሌክትራ

በአምላክ ስም ይሁንብህ አንተ እንግዳ! ከኔ አትውሰድብኝ።

ኦሬስቲስ

ያዘዝኩሽን አድርጊ። አትሳሳቺም።

ኤሌክትራ

በዘሮችህ ይሁንብህ! እጅግ ምወደውን ነገር አትዝረፈኝ።

ኦሬስቲስ

እንድትይዥው አልተውሽም።

ኤሌክትራ

ወይኔ ኦሬስተስ! ላለቅስልህ እንኳ አልቻልኩም።

ኦሬስቲስ

ምንም ሰቀቀን አያስፈልግም። ለማልቀስ መብት የለሽም።

ኤሌክትራ

ለሞተው ወንድም እንዳለቅስ ምንም መብት የለኝም?

ኦሬስቲስ

በሱ ስም ልትጠሪውም መብት ለሽም።

ኤሌክትራ

በፊቱ ይሄን ያህል ተዋርጃለኋ?

ኦሬስቲስ

ማንም አላዋረደሽም። ለቅሶ ላንቺ አይደለም።

ኤሌክትራ

አለብኝ። የያዝኩት የኦሬስቲስን በድን ከሆነ።

ኦሬስቲስ

ፈጠራ ካልሆነ በቀር የኦሬስቲስ በድን የለም።

ኤሌክትራ

እንግዲያውስ ያ ምስኪን ልጅ የት ነው የተቀበረው?

ኦሬስቲስ

የትም አልተቀበረም። ለህያው መቃብር የለም።

ኤሌክትራ

እንዴት አንተ ምን ማለትህ ነው?

ኦሬስቲስ

ምንም! እውነት አይደለም።

ኤሌክትራ

እና አልሞተም?

ኦሬስቲስ

አዎን! እኔ ካልሞትኩ

ኤሌክትራ

እና አንተ እሱ ነህ?

ኦሬስቲስ

ይህን የአባታችን ነበረውን የምልክት ቀለበት ተመልከች፡፡ እናም እውነት መሆኑን አረጋግጭ፡፡

ኤሌክትራ

ኦ! የተደሰትች ጸሀይ!!

ኦሬስቲስ

እኔም የተደሰትሽው ልበል፡፡

ኤሌክትራ

ድምጽህን ነው ምሰማው ?አውን ወዲህ መጣህልኝ?

ኦሬስቲስ

ከማንም ያልወጣውን የኔን ድምጽ ነው የምትሰሚው፡፡

ኤሌክትራ

እውነት ክንዶቼ አቀፉህ?

ኦሬስቲስ

ያውም ዳግም ላይለቁኝ!!

ኤሌክትራ

/ለማይሴናዊት/
እጅግ የተወደሽው ወዳጄ ኦሬስቲስ ይሄውና!ሞቷል የተባለው ሰው ይሄው ዳግም ተመለሰ፡፡

ማይሴናዊት

አየሁትኮ! እንባ ዐይኔን አረጠበው፡፡

ኤሌክትራ

እጅግ ምወደው አባቴ ልጅ! ዳግም ወዲህ መጣህልኝ።

ኦሬስቲስ

አዎን መጥቻለሁ። ግን እስከ ጊዜው በምስጢር ያዢው።

ኤሌክትራ

ለምን?

ኦሬስቲስ

ዝምታ ይሻላል። ውስጥ ያሉት ይሰሙናል።

ኤሌክትራ

የለም በድንግሊቱ አርጤምስ እምላለሁ። ውስጥ ያለችውን ሴት መፍራቴን አላቆምም። ምድር በአደጋ የተሞላ ነው።

ኦሬስቲስ

አዎን!

ኤሌክትራ

ወይኔ ሰቀቀኔን ቀሰቀስህብኝ!ምንም ስርየት አያጥበውም!ምንም መርሳት አያሸንፈውም!ምንም መስፈርት እስፈሪነቱን አይለካውም።

ኦሬስቲስ

እሱንም አውቀዋለሁ። ነገር ግን በነጻነት ስታወሪ የሆነውንም ማስታወስ ነው።

ኤሌክትራ

ለዘመናት ምላሶቼ ተቆልፈዋል። አሁን ከንፈሮቼን ለማላቀቅ ጊዜው ነው።

ኦሬስቲስ

እስማማለሁ! ነጻነትሽን ጠብቂያት!

ኤሌክትራ

እኮ ምን በማድረግ?

ኦሬስቲስ

አጋጣሚ ካልፈቀደ ምንም ቃል አትናገሪ።

ኤሌክትራ

አሁን አንተን አግኝቼህ ሳለ መናገርና መዘጋቱን ማን ሊያደራደርልኝ ይችላል? አወይ የቀድሞ ተስፋ! አወይ የቀድሞ ስሌት! ብቻ አሁን አገኘሁህ።

ኦሬስቲስ

አማልክት ሲያንቀሳቅሱኝ አንቺም አየሽኝ።

ኤሌክትራ

እንግዲያውስ አስቀድሜ ላደርገው የሚገባኝን አንተ ንገረኝ። አምላክ ወዲህ ከመለሰህ ይሄ መለኮታዊ ሃይል ነው።

ኦሬስቲስ

ደስታሽን ሳይ አመነታለሁ። ደስታሽ እጅግ በዛ ስልም ፈራለሁ።

ኤሌክትራ

ኦሬስቲስ አሁን ወዲህ መጥተሃል። በአመለም ከተደረጉ ጉዞዎች ሁሉ ያስደሰተኝ ጉዞ ይህ ነው። ኩብዙ ስቃይ በኋላ መጥተሃል። ግን እባክህ እንዲህ አታድርግ

ኦሬስቲስ

ምን አላድርግ?

ኤሌክትራ

ፊትህን አይቼ ከማገኘው ደስታ አትቀንሰኝ!

ኦሬስቲስ

እንኳን እኔው ልቀንስሽ ሌላ እንኳን ከፊቴ ልነጥልሽ ቢል እቆጣለሁ።

ኤሌክትራ

ትስማማለህ?

ኦሬስቲስ

አዎ

ኤሌክትራ

የኔ ውድ መቼም እሰማዋለሁ ብዬ የማልጠብቀውን ድምጽ ሰምቻለሁ። እስካሁን ምላሴ የተቆለፈ ነው።መጥፎ ዜና እንኳን ስሰማ አልጮህኩም ነበር።አሁን ግን አንተ አለኸኝ። መጥተህልኛል። በሰቀቀን የረሳሁትን ፊትህን አይቼዋለሁ።

ኦሬስቲስ

እናታችን ምንኛ እንደከፋች አትንገሪኝ። ኤጅስተስ በአባታችን ንብረት እንዴት እንደሚዘባነን አትንገሪኝ።ስለነዚህ ቃላት መነጋገር የጊዜን እድል ይቀንሳል። ከዚያ ይልቅ ይሄ ጠላቶቻችንን አቁለን የመጣንበት ሰበብ የሚከወንበትን መንገድ ብቻ ንገሪኝ። ወደ ውስጥ ሰስንገባ እናታችን ተደስተሽ እንዳታይሽ ተጠንቀቂ።ስኬታችን ላይ ስንደርስ ያሻሽን ያህል ደስታሽን ትገልጫለሽ።

ኤሌክትራ

ወንድሜ ደስታህ ደስታዬ ነው። ያለኝን ደስታ የሰጠኸኝ አንተ ነህ። ኤግስተስ እዚህ እንደሌለ ሰምተሃል። እናቴ ፊቴ እየሳቀ ታየኛለች ብለህ አትስጋ። አንተን በማየቴም ብቻ እንባዬ እንደሆነ መውረዱ አይቀርም።ሞተህ ካየሁህ በኋላ እንዴት መኖርህን ያውቃሉ? ለኔ መምጣትህ ተአምር ነው። በዚህ መሠረት አባቴ እንኳን ዳግም በህይወት ቢመጣ ምንም አልናገርም።

ኦሬስቲስ

ሽሽሽ! ዝም በይ አንድ ሰው ወዲህ ሲመጣ ሰማለሁ።

ፔዳጎጀስ

/እየገባ/
እናንተ ሞኞች!ምንም ሃሳብ የላችሁ? አደጋ ላይ መሆናችሁን አታውቁም? ከናንተ ቀድሞ እቅዳችሁ እዚህ ገባ። እኔ ብቻ መነሻውን ከውኛለሁ።መቆየት መደምሰስ ነው። ተግባራችንን ለመከወን ይሄ አጣዳፊው ሰዐት ነው።

ኦሬስቲስ

እንዴት አድርጌ ውስጥ ያለውን ተግባሬን ለመፈጸም እችላለሁ?

ፔዳጎጀስ

ደህና! አንተን ለማወቅ ምንም ዕድል የላቸውም።

ኦሬስቲስ

ሞቴን እንዳወጅህ ተረድቻለሁ።

ፔዳጎጀስ

አንተ በነሱ ዘንድ ሞተሃል።

ኦሬስቲስ

እናስ ተደሰቱበት! ምናሉ ሞቴን ሲሰሙ?

ፔዳጎጀስ

እሱን በመጨረሻ ነግርሃለሁ።

ኤሌክትራ

ወንድሜ ይሄ ሰው ማነው ንገረኝ?

ኦሬስቲስ

አላወቅሽውም?

ኤሌክትራ

መገመት እንኳን አልቻልኩም።

ኦሬስቲስ

በእጁ አሳልፈሽ የሰጠሽኝን ሰው ምን አታስታውሺም?

ኤሌክትራ

ምን! ይሄ ሰው እሱ ነው?

ኦሬስቲስ

ባንቺ እጅና በሱ ሩቅ ሃሳብ ወደ ፎዝያውያን ምድር ሄድኩ።

ኤሌክትራ

አባቴ በሞተበት ዘመን ከአገልጋች ሁሉ ታማኝ ሆኖ የተገኘው ይህ ሰው ነው?

ኦሬስቲስ

እሱ ነው። ምንም ጥያቄ የለውም።

ኤሌክትራ

አቤት አንተ ታማኝ ሰው።እንዴት ተቀይረህ መጣህልኝ! አቤት! እንዴት የተወደዱ እጆች ነው ያሉህ! አይቼ እንኳን እንዳልለይህ ምንም ምልክት የለህም! መጀመሪያ ስትመጣ እጅግ መልካም ዜና ይዘህልኝ ግን በቃልህ ገድለኸኝ ነበር። የተባረክህ ሁን። በአንተ ውስጥ አባቴን አያለሁ። በአንዴ እጅግ ጠልቼህ ዳግም እጅግ ወደድኩህ!

ፔዳጎጅስ

ይበቃል። ይመስለኛል።ነገሩን ሁሉ በግልጽ ለመናገር ወደ ፊት ብዙ ቀንና ሌሊት አሉን። አሁንግን እዚህ በቆማችሁበት እድልህን ለመጠቀም ጊዜህን ተጠቀም። ክላይቴምኔስትራ ብቻዋን ናት። ማንም ሰው አብሯት የለም።አሁን ከዘገየህ በኋላ እድል አይኖርህም።

ኦሬስቲስ

ከማንኛውም ጊዜ መፍጠን አለብኝ። አማልክት ስኬት እንዳገኝ ይርዱኝ።
/ይገባል/

ኤሌክትራ

/ለአፖሎ ምስል ትጸልያለች/
አፖሎ ጆሮህን ስጠው።የኔንም ጸሎት ስማኝ። እነሆ በጉልበቴ ተንበርክኬ እለምንሃለሁ። እቅዳችንን አሟላ። እባክህን ቸር ሁንልን። እቅዳችንን ለማሟላት ርዳን።

ማይሴናዊት

የጦር አምላክ ቁጣን እየተነፈሰ ወዲህ  ሲመጣ አያለሁ።

ኤሌክትራ

ተወዳጇ እህቴ አሁን ተግባሯን የሚፈጽምበት ነው። ዝም ብለሽ ጠብቂው።

ማይሴናዊት

ምን ማለትሽ ነው ምን እያደረጉ ነው?

ኤሌክትራ

እሷ ሳጥኑን ልትቀብር ትዘጋጃለች። እሱ ደግሞ ከጎኗ ቆሟል?

ማይሴናዊት

ለምንድነው ወደ ውስጥ የምትሯሯጥኚው?

ኤሌክትራ

ኤጅስተስ ሳይታሰብ ወዲህ እንዳይመጣ ሊተብቀው ነው።

ክላይቴምኔስትራ

/ከውስጥ/
አረ የሰው ያለህ! ተከድቻለሁ!

ኤልክትራ

አንድ ሰው እየጮኸ ነው ትሰሚያለሽ?

ማይሴናዊት

የምሰማው ለጆሮ ሚቀፍ ሰቀቀን ነው።

ክላይቴምኔስትራ

/ከውስጥ/
ወይኔ! ኤጅስተስ የት ነህ?

ኤሌክትራ

ይሄው ያው ድምጽ ተደገመ።

ማይሴናዊት

የምሰማው ለጆሮ ሚቀፍ ሰቀቀን ነው።

ክላይቴምኔስትራ

/ከውስጥ/

ልጄ! ልጄ! እናትህን እዘንልኝ።

ኤሌክትራ

ለሱም ሆነ ለወለደው አባቱ አንቺ አላዘንሽም።

ክላይቴምኔስትራ

/ከውስጥ/
ወይኔ! ተወጋቻለሁ!

ኤልክትራ

ብርታት ካለሽ ዳግም ተነሽ!

ክላይቴምኔስትራ

/ከውስጥ/
አህ! አሁንም በድጋሚ!

ኤሌክትራ

ምነው ኤጅስተስ አብሮሽ በሆነ።

ማይሴናዊት

እርግማኖች ተፈጽመዋል። ከመሬት በታች የዋሉት ዳግም ህያዋን ሆነዋል።

ኤሌክትራ

ኦሬስቲስ! እንዴት ሆነልህ?

ኦሬስቲስ

ከውስጥ ያለው በመልካም ተፈጽሟል። አፖሎ እንዳዘዘው

ኤሌክትራ

እርጉሟ ሞተች?

ኦሬስቲስ

ከእንግዲህ ምንም አትፍሪ። የምታዋርድ እናት የለሽም።

ማይሴናዊት

ቆይ! ቆይ! ኤጅስተስ እየመጣ ነው።

ኤሌክትራ

ኦሬስቲስ ወደ ውስጥ ተመለስ።

ኦሬስቲስ

በጉልበታችን ስር ነው።

ኤሌክትራ

በደስታ ነው የሚራመደው።

ማይሴናዊት

በተቻለህ ፍጥነት ወደ ውስጥ ግባ። አንደኛውን ፈጽመሃል አንዱ ደግሞ ይቀርሃል።

ኦሬስቲስ

ምንም አያሳስብሽ እወጣዋለሁ!

ኦሬስቲስ

ከውስጥ ያለው በመልካም ተፈጽሟል። አፖሎ እንዳዘዘው

ኤሌክትራ

ወደ ነበርክበት ተመለስ።

ኦሬስተስ

ይሄው ! እደበቃለሁ
/ራሱን ይደብቃል/

ኤሌክትራ

እዚህ ያለውን ለኔ ተውልኝ።

ማይሴናዊት

ቅን ፍርድ እንደሚጻረረው ሳያውቅ የሰማው ጥቂት ወሬ አስደስቶት ይገሰግሳል።

ኤጅስተስ

/እየገባ/

ማንኛችሁ ናችሁ ፎኔቨ ያዊው የት እንዳለ የምታውቁት? ኦሬስተስ በሰረገላ ውድድር የመሞቱን ዜና እንዳጣልኝ ሰምቻለሁ።አንቺ እዚያ የቆምሽው! አዎ አንቺን ማለቴ ነው! አንቺ! አንቺ!ነገሩ አንቺን ነው የሚመለከተው ስለዚህ አንቺ ንገሪኝ።

ኤሌክትራ

አዎን አውቃለሁ። ምናለ ባልሆነ ኖሮ!

ኤጅስተስ

እንግዲያውስ እንግዳው ወዴት እንዳለ ንገሪኝ።

ኤሌክትራ

ቤት ውስጥ ነው! አስተናጋጇንም ደግ ሆና አግኝቷታል።

ኤጅስተስ

እናስ መሞቱን አስረግቶ ተናግሯል?

ኤልክትራ

ከመናገር የተሻለ በድኑንም ይዞ መጥቷል።

ኤጅስተስ

እና አስከሬኑን ፊት ለፊት ማየት እችላለሁ?

ኤሌክትራ

በትክክል ትችላለህ። አስቀያሚ እይታ ነው።

ኤጅስተስ

ያልሽው አስደስቶኛል። ያልተለመደ ነገር።

ኤሌክትራ

እዚህ ብታገኘው ልትደሰት ትችላለህ።

ኤጅስተስ

ዝም በይ! በሩ እንዲከፈት አዛለሁ። ስለዚህም መላው ማይሴናዊ የጠላቴን ሞት ያውቃል። የጠላቴን አስከሬን በእጇ ነደብደብና ስሜቱን ማወቅ እሻለሁ።

ኤሌክትራ

ሁሉንም ነገር አጠገቤ ይዤዋለሁ። ከእንግዳው ጋር ተስማምቼ አመዱን ወስጄዋለሁ።

ኤጅስተስ

/ሳጥኑን እያየ/
ዚዩስ! በአማልክት ፈቃድ የሆነውን አይቻለሁ።ይሄንንም ማለት ካልኖረብኝ በኔምሲስ ስም እተወዋለሁ። ሁሉም ሰው ያየው ዘንድ ሽፋኑን ከላዩ አንሱት።

ኦሬስቲስ

አንተው ራስህ አንሳው። ይህ በድን የኔ አይደለም። ያንተ ነው።

ኤጅስተስ

እውነት ነው! ይሄንን እቀበላለሁ። እቤት ውስጥ ካለች ክላቴምኔስትራን ትጠራታለህ?

ኦሬስቲስ

አጠገብህ ናት! እሷን ፍለጋ የትም መሄድ አያሻህም።

ኤጅስተስ

/የክላይቴምኔስትራን በድን ይፋጠጣል/
ምንድነው የማየው ነገር?

ኦሬስቲስ

የምትፈራውን ነገር። ይህንን ፊት አታውቀውም?

ኤጅስተስ

ለመሆኑ በሞት ጥለ የጠለልከን አንተ ማን ትሰኛለህ?

ኦሬስቲስ

ሞቱ ያልካቸው ሰዎች በህይወት ዳግም ሲኖሩ አይተህ ታውቃለህ?

ኤጅስተስ

ገባኝ! አንተ ምትናገረኝ ኦሬስቲስ ብቻ ነው ልትሆን ምትችለው። ይሄ መጨረሻዬ ነው። አንድ ቃል ብቻ አናግረኝ።

ኤሌክትራ

አንድም ቃል! ወንድምዬ አደራህን አንድም ቃል አታናግረው። ሰዎች በሞታቸው ቋፍ ላይ ካሉ ጊዜ መስጠት አይገባም። በቻልከው ፍጥነት ግደለው። ከቀድሞው ስቃዬ ሁሉ ሚገላግለኝ ይሄ ብቻ ነው።

ኤጅስተስ

ታዲያ ለምን ወደ ውስጥ? የምሰራው ስራ ፍትሃዊ ነው ካልክ ለምን ጨለማን መረጥክ? እጆችህ ለምን እዚህ ሊገድሉኝ አልቻሉም?

ኦሬስቲስ

የመሞቻህን ስፍራ አንተ አይደለም የምትመርጠው። አባቴን በገደልክበት እንድትሞት ነው የምፈልገው።

ኤጅስተስ

እንግዲህ ይሄ ቤት የፔሎፔዲያውያንን መከራ ለማስተናገድ ተመርጧል ልበል?

ኦሬስቲስ

አሁን ደግሞ ያንተን ያያል። እጅግም ቢያን ያንተን ያያል።

ኤጅስተስ

አባትህ የምታወራለትን ዓይነት ሰው አይደለም

ኦሬስቲስ

ብዙ ዝብዝብ አበዛህ። ሞትህን ከማየት ዘገየህ።

ኤጅስተስ

እንግዲያው መንገዱን ምራኝ።

ኦሬስቲስ

ግዴለም አንተ ቅደመኝ።

ኤጅስተስ

እንዳላመልጥህ ፈራኸኝ?

ኦሬስቲስ

ፍጹም እንደሱ አይደለም። ግን ምንም ቢሆን እንደፈቃድህ አትሞትም። ሞትህ እጅግ የመረረ እንዲሆን አብዝቼ እጠነቀቃለሁ። አቤት የአትሪዩስ ዘሮች። በዚህ የፍትህ ቀን ተግባር በቁጣ ነጻ እስከወጣችሁ ድረስ ምን ያህል ተሰቃይታችኋል!!
ፍትህ ከህግ በላይ በሚሆኑት ሁሉ በስርዓት ትሰጣለች።ፍትህን በሞት!